# የአማርኛ ፡ መጽሔተ ቃላት ።

መስፍን ልሳኑ ።

ባለ አንድና ባለ ኹለት ፊደላት ።

መጀመሪያ ክፍል ።

ተሐትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳ወ፬ቱ ዓመተ መንግሥቱ
ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፵፯ ዓ . ም .

በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ ። ቍ [illegible]

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

« ------ የሀገራችንን ትምህርት በአማርኛና በግዕዝ መማር ትልቅ ጥቅም ያለበት ነው ----------

--------- የሀገራችንን ትምህርት ሳንማር የውጭ ሀገር ትምህርት እማራለኹ ማለት በድቡሽት ላይ ቤት እንደ ሠራው ሰው ምሳሌ ለመኾን ነው ።»

ቀ . ኃ . ሥ .

«ልጅነት የያዘው ምላሳችን መንካ
ከቋንቋችን በፊት ሌላ ቋንቋ አይንካ

ግዕዝ ካማርኛ አስተባብሮ ሲያውቅ
ከውጭ ሀገር ቋንቋ ያን ጊዜ ይንጠቅ ።»

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ።

## ሦስተኛው ጉዳና ።

ይኸ ጉዳና ከመጀመሪያው ጋራ ይተባበራል፤ ነገር ግን ግዕዛኑን በመላ አስቀድሞ ሌሎቹንም እንደየማዕርጋቸው እያከታተለ በደኅና አኳኋን ከተጓደደ በኋላ ከቃላት ብዛት ማጠር የተነሣ አካኼዱ ስለሚሳከር ካገልግሎት ታግዶአል ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ | ለየ | ለመነ | ለመለመ | ተመለከተ |
| ለ | አሸ | ለመደ | ለመዘገ | ተመረኰዘ |
| ሐ | አገዘ | ለመጠ | ለመጠጠ | አመሰገነ |

በተገለጸው ማስረጃ መሠረት በመልካም አኳኋን መከናወን ከጀመረ በኋላ ባለ ሥድስት ፊደላትና ከዚያም በላይ ወደ ኾኑት ቃላት ሲደርስ መሳከሩን ተመራማሪ ጉዳናውን ተጠቍሞአልና ቢፈልግ ይድረስበት ።

## አራተኛው ጉዳና ።

ይኸ ጉዳና እያሌውን ጊዜያት የአውሮጳውያን መጽሐታተ - ቃላት የሚዘጋጁበት ነው ። የፊደላትን ተራ ብቻ የሚጠብቅ ሲኾን ያማርኛን ቃላት በእርግጠኛ ባሕርያዊ ሥነ ጽሑፋቸውና አነባበባቸው ለመወሰን የማይችል በመኾኑ ላማርኛችን ጠቃሚ ስላልኾነ አገልግሎቱን ፈላጊዎች ከመኾን ታገድን ።

ጉዳናውም መነሻቸው ሀ በኾኑ ቃላት ከዚኽ በታች ተገልጾአል ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀገር | ሁከት | ? | ሃሌ | ? | ህላዌ | ሆሣዕና |
| ሀሁ | ሁዳዴ | ? | ሃይ | ? | | ሆይ |
| ሀብት | ሁዳድ | ? | ሃይማኖት | ? | | ሆድ |

ምሳሌ ፤ ማርና ወተት ምን አገናኝቶት ባይ ከኾነ ፤ ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ እንደ ሚባለው ኹሉ ያማርኛ መጽሐተ - ቃላት የቃላትን ባሕርያዊ ሥነ ጽሑፋቸውን አነባ በባቸውንና ተራቸውንም በጠነቀቁ ፤ በተመለከቱ በሦስት ዐይነት ታላላቅ ጉዳናዎች ሊዘጋጅ ሲችል ፤ ማርን አምርሮ ወተትን አጥቍሮ ፤ ይኸን አማርኛችንን መወሰን የማይችል አራተኛውን ጉዳና መምረጥ በቋንቋችን ላይ ከሚጥለው እንከን ይልቅ ተፈጥሮን ካለማወቅ አያስቈጥርምን ? ።

## አ ።

የአ ፊደል እንዳይዋጥ ምንም እንኳ ከዚኽ በፊት የታሰበበት ቢኾን ጊዜያትን በሚያመለክቱ አናቅጽ መድረሻ ላይ ካልኾነ በስተቀር ይኸ አስተያየት እንዲጸና ማድ ረግ አጥጋቢ አይደለም ፤ እንዲረጋ ከተፈለገ ግን ያማርኛ አጻጻፍ ይለወጥ ከማለት ያደ ርሳል ። ይኸንኑም ከዚኽ በታች በተገለጸው ማስረጃ መመልከት ነው ።

| የቀለጠፈው ። | | መሠረት ። |
|---|---|---|
| ባላምበራስ | = | በአለአምባራስ |
| እያከታተለ | = | እየአከተአተለ |
| ማባበል | = | መአበአበል |

ከዚኽም በላይ ጥንት በግዕዛን ፊደላት ብቻ ይነገር እንደ ነበረ ወደ ማስተዋል ያዘነበልን እንደ ኾነ ከሚቀጥለው አስተያየት እንደርሳለን ።

| የቀለጠፈው ። | | መነሻው ። |
|---|---|---|
| መስፍን | =መሰእፈእነእ= | (መ) ሰፈነ |

## ማስገንዘቢያ ።

ሰባቱን ማዕርጋተ - ፊደላት በመጠበቅ ፤ የፊደላትን ተራ በመጠንቀቅ ፤ የቃላትን አነባበብ በማመልከት ፤ ያማርኛን ባሕርያዊ ሥነ ጽሑፍ በማጽናት ላይ ያለውን ሐተታ ፤ የእንስሳት ፤ የአራዊት ፤ የዕፀዋት ፤ የአዕዋፍ የቈሳቍስ ፤ እነዚኽንም የመሳሰሉት ፤ በጠቅላላ ፍጥረታቸው ለሥዕል የሚመቹትን ኹሉ በመግለጽ ፤ ከውጭ አህጉር የተወረሱትን ቃላት በማከል ፤ ተዘጋጅቶ በሚወጣው መጽሔተ - ቃላት ውስጥ እየተነተንን በማስረጃም እያጸደቅን ሥራችንን ለማጽናት ፤ እንዲዘገይ ተደርጎአል ።

## መጠቈሚያ ።

(ሀ) ባናታቸው ላይ ይዘት (.) የተደረገባቸው ፊደላት ከቅንጃቸው ጋራ ተናብበው መጥበቃቸውን ይገነዘብዋል ለማ ።

ባናታቸው ላይ ድርብ ስረዝ (‥) የተደረገባቸው ፊደላት ከቅንጃቸው ጋራ ተናብበው በፍጥነት እነጋገር መጥበቃቸውን መገንዘብ ነው ። ብስ ።

፡

በኹለት ነጥብ (፡) የተመለከቱት ሳይናበቡ የሚጠብቁ ናቸው ። ጥገ ።
ያልተመለከቱት ግን እየተናበቡ እንደ ፊደሉ ደንብ የማይጠብቁ ናቸው ።

(ለ)=በዚኽ እኩያነትን ፤ እኩልነትን በሚገልጽ ምልክት የተመለከቱት ኹሉ ፍቾቻቸው ያው ነው ።

(ሐ) ※ ይኽ ምልክት ፤ ቃሉ ኹለት ፍች እንዳለው ይገልጻል ።

# መሠረታዊ የአማርኛ ፊደል ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ቡ | ጊ | ዳ | ሄ | ው | ፆ |
| በ | ጉ | ዷ | ሃ | ዌ | ዝ | ሖ |
| ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ሕ | ሾ |
| ዶ | ሁ | ዊ | ዛ | ሔ | ሽ | ጠ |
| ሀ | ዉ | ዚ | ሓ | ሼ | ጥ | ዮ |
| ወ | ዙ | ሒ | ሻ | ጤ | ይ | ቾ |
| ዘ | ሑ | ሺ | ጣ | ዬ | ቸ | ኮ |
| ሐ | ሹ | ጢ | ያ | ቼ | ክ | ሎ |
| ሸ | ጡ | ዩ | ቻ | ኬ | ል | ኞ |
| ጠ | ዪ | ቺ | ካ | ሌ | ኝ | ሞ |
| የ | ቹ | ኪ | ላ | ኜ | ም | ኖ |
| ቸ | ኩ | ሊ | ኛ | ሜ | ን | ሦ |
| ከ | ሉ | ኚ | ማ | ኔ | ሥ | ኾ |
| ለ | ኙ | ሚ | ና | ሟ | ኽ | ዖ |
| ኘ | ሙ | ኒ | ሣ | ኼ | ዕ | ፎ |
| መ | ኑ | ሢ | ኻ | ዔ | ፍ | ዡ |
| ነ | ሡ | ኺ | ዓ | ፌ | ዥ | ጾ |
| ሠ | ኹ | ዒ | ፋ | ዤ | ጽ | ቆ |
| ኸ | ዑ | ፊ | ዠ | ጼ | ቅ | ጆ |
| ዐ | ፉ | ዢ | ጻ | ቂ | ጅ | ፆ |
| ፈ | ዡ | ጺ | ቃ | ጄ | ዕ | ጬ |
| ዠ | ጹ | ቁ | ጃ | ፂ | ጯ | ኗ |
| ጸ | ቁ | ጂ | ፃ | ጩ | ኀ | ሶ |
| ቀ | ጁ | ፂ | ጫ | ኄ | ስ | ጿ |
| ጀ | ፁ | ጪ | ኃ | ሴ | ጵ | ሮ |
| ፀ | ጩ | ኂ | ሳ | ጴ | ር | ቶ |
| ጨ | ኁ | ሲ | ጳ | ሬ | ት | ፖ |
| ኀ | ሱ | ጲ | ራ | ቴ | ፐ | አ |
| ሰ | ጱ | ሪ | ታ | ፔ | እ | ቦ |
| ጰ | ሩ | ቲ | ፓ | ኤ | ብ | ጎ |
| ረ | ቱ | ፒ | ኣ | ቤ | ጓ | ዶ |
| ተ | ፑ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ |
| ፐ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ሀ | ዎ |

## ሕፁፃን ማዕርግ ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጐ | ኵ | ቋ | ኌ | ጕ |
| ኰ | ቈ | ኋ | ጔ | ኵ |
| ቌ | ኍ | ጓ | ኴ | ቍ |
| ኈ | ጐ | ኳ | ቋ | ኍ |

## ማስገንዘቢያ

ደጅ ጠኛዎች

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኧ | ? | ? | ? | ? | ? | ? |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

፪/ ዲቃሎች

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |

፫/ ኘ ኙ ኚ ኛ ኜ ኝ ኞ

፬/ ፐ ፤ በኋላ ዘመን የመጣ የአውሮ ጳውያን ፊደል ሲኾን በዘልማድ የጰን ቦታ ለመንጠቅ ይፍጨረ ጨራል ።

ፐ ፑ ፒ ፓ ፔ ፕ ፖ

## ማሳሰቢያ ።

አማርኛ ከግዕዝ ፤ ግዕዝም ከእብራይስጥና አዓረ ብኛ የተመሠረተ ነው ። ይኸ ሲኾን ከግዕዙ ይልቅ አማርኛ ከዕብራይስጡ ጋራ የቅርብ ዝምድና አለው ። ይኸንኑም እነ ፤ ሸ ፤ ኸ ፤ ባማርኛ ውስጥ ያላቸውን አገላግሎት በመመልከት ይረድዋል ። ይኸ መሠረታዊ ያማርኛ ፊደል ከዕብራይስጡ ፊደል ጋራ በቅደም ተከተል እምብዛም የማይለያይ በመኾኑ ባገልግሎት ውስጥ እንዲውል መስማማት እውነተኛ ሕግን የተ መረኰዘ ጥቅምን አስከታይ ነው ።

# አ ኀ ዝ ።

| | | |
|---|---|---|
| | አ ል ቦ | 0 |
| ፩ | አንድ | 1 |
| ፪ | ኹለት | 2 |
| ፫ | ሦስት | 3 |
| ፬ | አራት | 4 |
| ፭ | አምስት | 5 |
| ፮ | ሥድስት | 6 |
| ፯ | ሰባት | 7 |
| ፰ | ስምንት | 8 |
| ፱ | ዘጠኝ | 9 |
| ፲ | ዓሥር | 10 |
| ፳ | ኻያ | 20 |
| ፴ | ሠላሳ | 30 |
| ፵ | አርባ | 40 |
| ፶ | ሓምሳ | 50 |
| ፷ | ሥሳ | 60 |
| ፸ | ሰባ | 70 |
| ፹ | ሰማንያ | 80 |
| ፺ | ዘጠና | 90 |
| ፻ | መቶ | 100 |
| ፲፻ | ሺሕ | 1000 |
| ፼ | እልፍ=ዓሥር ሺሕ | 10,000 |
| ፲፼ | አእላፍ=መቶ ሺሕ | 100,000 |
| ፻፼ | አእላፋት | 1,000,000 |
| ፲፻፼ | ትእልፊት | 10,000,000 |
| ፼ ፼ | ምእልፊት | 100,000,000 |
| ፲፻ ፼ ፼ | አእላፈ-አእላፋት | 100,000,000,000 |
| ፼ ፼ ፼ | አእላፈ-ትእልፊት | 1,000,000,000,000 |
| ፲፼ ፼ ፼ | ትእልፊተ-አእላፋት | 10,000,000,000,000 |
| ፻፼ ፼ ፼ | ምእልፊተ-አእላፋት | 100,000,000,000,000 |
| ፲፻፼፼፼ | ትእልፊተ-ምእልፊት | 1,000,000,000,000,000 |
| ፼ ፼፼፼ | ምእልፊተ-ምእልፊት | 10,000,000,000,000,000 |

በሦስተኛው ዓምድ የተገለጠው አኀዝ በመሠረቱ ዓረብኛ ነው ።

በዛሬው ዘመን ፤ በሒሳብ ረገድ እጅግ በጣም አስፈላጊ በመኾኑ ያገለግለን ዘንድ ከአማርኛው አኀዝ ጋራ እየተነጻጸረ ተጽፎአል ።

<u>ማስገንዘቢያ ።</u> ፼=እልፍ=መቶ ጊዜ መቶ ማለት ነው ።

# የአማርኛ መጽሔት ቃላት ።

| | |
|---|---|
| **ሀ ሀ** | ያማርኛ ፊደላት መወጠኛ ። ሀ፤ ሳይሉ ጽሕፈት ውል ሳይዙ ሙግት ። ፩/ የግዕዛን ፊደላት መጀመሪያ ። ሀ፤ ባሉ ደሞዝ በሉ ። ፪/ ሀብት = ሀብት ። ፫/ ስሙ = ሃሌታው ሀ ። ሀብት ውሂብ ሃይማኖት ቡሄ ወህኒ ሆይ |
| **ለ ለ** | የሀ ተከታይ ። ፩/ መስተዋድድ ። ለወገኑ ሰጠ ። ለአባቱ ላከ ። ለቤት ሣንቃ ለሰው አለቃ ። ለራስ ምታት ጬኽበት ለሆድ ቍርጠት ብላበት ። ለሚስት ያጐርሰዋል ለተመታ ይክሰዋል ። ፪/ በአናቅጽ አርእስት ላይ እየተጫነ፤ አድራጊነትን አስደራጊነትን፤ ተደራጊነትን፤ ተደራራጊነት፤ አደራራጊነትን፤ አዳራጊነትን፤ ተደራጊነት፤ ይገልጻል ። ለመሥራት የሚደፍር መብላትን አይደፍርም ። ለማስገደል ነው ። ለመገደል ነው ። ለመገዳደል ነው ። ለማገዳደል ነው ። ለማጋደል ነው ። ለመጋደል ነው ። ፫/የበጎ ማድረጊያ ። ፈቀደለት ። ፈረደለት ። ፬/ ለብሰ = ለበሰ ለየ ሉድ ሊባ ላላ ሌባ ልጥ ሎጥ ። |
| **ሐ ሐ አ** | ሦስተኛ ። ፩/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ፪/ ሐውልት = ሐውልት አጌ = ሐጌ ። ፫/ ስሙ = ሐመሩ ሐ ። ሐውልት እሑድ ሒሳብ ሐሳብ እግዚአብሔር ሕዝብ ብሖር |
| **መ መ** | አራተኛ ። ፩/ የአናቅጽ አርእስት መነሻ ። መምጣት፤ መኼድ ። መለመን የለመደ ምላስ በሕልሙ አቁማዳን ይዋስ ። ፪/ መስቀል = መስቀል መጣ ሙዳ ሚና ማማ ሜታ ምሳ ሞራ |
| **ሠ ሠ** | አምስተኛ ። ፩/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ሴት ። ሤት ። ፪/ ሠርሐ = ሠራ ። ፫/ ስሙ ንጉሡ ሠ ። ሠራ ንጉሠ መሢሕ ሣለ ሤት ሥራ ሦስት |
| **ረ ረ** | ሥድስተኛ ። ፩/ ረብሐ = ረባ ። ረባ ሩብ ሪቅ ራራ ሬት ርግብ ሮሮ |
| **ሰ ሰ ዘ** | ሰባተኛ ። ፩/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ሳለ ። ሣለ ። ፪/ ሰማይ = ሰማይ ተዝካር = ተስካር ። ፫/ ስሙ = እሳቱ ሰ ። ሰባ ሱቲ ሲራክ ሳተ ሴት ስስ ሶራ |

| | |
|---|---|
| **ሸ ሠ ሰ** | ስምንተኛ ። ፩/ መድረሻቸው ሠ፤ ሰ ለኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ነገሠ - ነጋሽ፤ መናገሻ፤ መንገሻ ። ካሳ - ከሽ፤ መከሻ ። ፪/ ሢመት = ሹመት ። ሲበት = ሽበት ። መስየ = መሸ ። ሸተ ሹም ሺሕ ሻጣ ጋሼ ቀዳሽ ሙሾ |
| **ቀ ቀ** | ዘጠነኛ ። ፩/ ቀብዐ = ቀባ ቀባ ቁና ቂጣ ቃታ ቄራ ቅል ቆዳ |
| **በ በ መ** | ዓሥረኛ ። ፩/ መስተዋድድ ። (ሀ) የማድረጊያ ። በዱላ ቀነደበው ። (ለ) የቦታ ። በተራራው ላይ አለፈ (ሐ) የጊዜ ። በሥድስት ሰዓት ይመጣል ። (መ) አመዛዛኝ ። ባለፈ ነገር አትቈጭ ። ፪/ ያናቅጽ ባዕድ መነሻ (ለጊዜያት) ። በተሰበረ ። በተሰበረ ነበር ። በመጣ ኖሮ ። ፫/ ስለ ። በእገሌ በሞቱ ። ፬/ በልዐ = በላ ። ዘንመ = ዘነበ ። በመድሎት ልቡ = በልቡ ሚዛን ። በላ ብቡ ቢያ ባላ ቤት ብዙ ቦይ ። |
| **ተ ተ** | ዓሥራ አንደኛ ። ፩/ የተደራጊና የተደራራጊ የተደራጊም፤ መመደቢያ ። ተገደለ ። ተገዳደለ ። ተጋደለ ። ፪/ከ ። ተኵል = ከእኩል ። ፫/ ተከለ = ተከለ ። ተላ ቱር አላቲ ታታ ስታቴ ትል መቶ ። |
| **ቸ ተ ኀ፤ ክ ህ** | ዓሥራ ኹለተኛ ። ፩/ መድረሻቸው፤ ተ፤ ለኾኑ፤ አናቅጽ፤ ቅጽልን ። መወሰኛ ። ዛተ - ዛች፤ መዛቻ፤ ዛቻ ። ፪/ በልኣት = በላች ። ኄር = ቸር ። ክህለ = ቻለ ። ቸከ ምቹ ቡቺ ቻለ ልቼ ችኮ ቀበርቾ ። |
| **ኀ ኀ** | ዓሥራ ሦስተኛ ። ፩/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ድኅነት ። ድኽነት ። ፪/ ኅብል = ኅብል ። ፫/ ስሙ = ብዙኃኑ ኀ ። ኅብል ድኍር ኂሩት ኃይል ርኅራኄ ኅዳር ኆኅት ። |
| **ነ ነ ሐ** | ዓሥራ አራተኛ ። ፩/ ነገር = ነገር ። ዋሕድ = ኣንድ ። ነጋ ኑግ ወህኒ ወህኒ ናዳ ብያኔ ንጉሥ ኖረ |
| **ኘ ነ** | ዓሥራ አምስተኛ ። ፩/ መድረሻቸው፤ ነ፤ ለኾኑ፤ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ዳነ - ዳኝ፤ መዳኛ ። ፪/ አስትየኒ = አጠጣኝ ። ዳን = ዳኛ ። ሸኘ መናኙ መጣ ሸኚ ተኛ ዳኘ ድኝ አኞ |

| | |
|---|---|
| **አ አ ሀ፤ ሐ፤ ኀ** | ዓሥራ ሥድስተኛ ። ፩/ የአናቅጽ ባዕድ መነሻ (አድራጊነትን የሚገልጽ) ። ፈገፈገ - አፈገፈገ ። መጣ - አመታ ። ፪/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። አረፋ ። ዓረፋ ። አርብ ። ዓርብ ። ፫/ ሀለሌ ። አለሌ ። ሐለመ = አለመ ። ኀዘለ = አዘለ ። ፬/ ስሙ = አልፋው አ፤ አለ ኡኡ ኢትዮጵያ አሳብ ኤል እርሱ ኦሃ |
| **ከ ከ ኀ፤** | ዓሥራ ሰባተኛ ። ፩/ መስተዋድድ ። (ሀ) የመነሻ ። ከበረሃ ተመለሰ ። (ለ) የቦታ ። ከቤቱ በላይ ነው ። (ሐ) የጊዜ ። ከሰዓት በላይ ይመጣል ። ፪/ መስተፃምር ። (ሀ) የውልና ። የምክንያት ። ከመጣ ይሰጠዋል ። ከወደደ ዘንድ ይማር ። (ለ) የጊዜ ። ከቈረበች አፈረሰች ። ከመነኰሰች ባሰች ። (ሐ) አመዛዛኝ ። እኔ ከሞትኩ አይብቀል አለች አህያ ። ፫/ ተ ተወፈሩ ሰው አይፈሩ ። ተከፉ ጐረቤት አይሠሩም ደኅና ቤት ። ፬/ ከፈለ = ከፈለ ። ብኍዕ= ቡኮ ። ከፋ ኩታ ኪስ ካባ ዘኬ ክር ኮባ |
| **ኸ ከ** | ዓሥራ ስምንተኛ ። ፩/ በላእኩ = በላኹ ። ሦከ = እሾኽ ። ፪/ ስሙ = ኹነኛው ኻ ። ቸኽ ኹለት ኺድ ኻያ ኼድ በላኽ ኾነ |
| **ወ ወ መ፤** | ዓሥራ ዘጠነኛ ። ፩/ ወለደ = ወለደ ። መንበር = ወንበር ። መንጠፍት = ወንጠፍት ። ወዛ ዉሎ ልባዊ ዋልታ ህላዌ ውሻ ቢላዎ |
| **ዐ ዐ** | ኻያኛ ። ፩/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። አረፋ ዓረፋ ። ፪/ ዓለም = ዓለም ። ዕዉር ። ፫/ ስሙ = ዓይኑ ዐ ። ዐበደ ዑደት ዒሣ ዓሣ ሱባዔ ሥዉር ተጸውዖ |
| **ዘ ዘ የ፤** | ኻያ አንደኛ ። ፩/ ዘርፍ አያያዥ ። ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ = የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ። ፪/ ዘርአ = ዘራ ። ረየመ = ረዘመ ። ዘባ ዙሃ እግዚአብሔር ዛፍ ዜጋ ዝና ዞማ |
| **ዠ ዘ** | ኻያ ኹለተኛ ። ፩/ ዝእብ = ዥብ ። ዠዥ ዡዋ ዢዠት ጋዣ አጋዤ ዥብ ዦንዦ |
| **የ የ ዘ፤** | ኻያ ሦስተኛ ። ፩/ ዘርፍ አያያዥ ። ዘርቤተ ሰላም ነጸፈ = የፍቅርን ምንጣፍ አነጠፈ ። ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ = የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ። የመነኵሴ ሎሌ ። የክረምት አሞሌ ። የመስከረም |

| | |
|---|---|
| | ውስጡ በጋ ያረመኔ ልቡ ቀጋ ።፪/ ዮሐንስ = ዮሐንስ ። ረየመ = ረዘመ ። የት መዩ የዪ ያያ ቀዬ ይኽ ዮሐንስ ። |
| **ደ ደ** | ኻያ አራተኛ ። ፩/ ደክመ = ደከመ ። ደማ ዱዳ ዲብ ዳቤ ነጋዴ ድባ ዶግ |
| **ጀ ደ** | ኻያ አምስተኛ ። ፩/ እድ = እጅ ። ዳን = ጃን ። ባጅ የጁ ቅጂ ጃኖ ወስጄ እጅ ቈንጆ |
| **ገ ገ** | ኻያ ስድስተኛ ። ፩/ ገዘረ = ገረዘ = ገዘረ ። ገባ ጉድ ጊዮርጊስ ጋዳ ጌታ ግራ ጎታ |
| **ጠ ጠ ጸ፤ ፀ** | ኻያ ሰባተኛ ። ፩/ ጠል = ጠል ። ወጽአ = ወጣ ። ሐፁር = ኣጥር ። ጠባ ጡት መናጢ ጠፋ ጤዛ ጥጥ ጦጣ |
| **ጨ ጠ ጸ፤ ፀ፤ ቀ የ** | ኻያ ስምንተኛ ። ፩/ ጤሰ = ጨሰ = ጤሰ ። ጸልመ = ጨለመ ። ፄው = ጨው ። ረቀየ = ረጨ ። ጨሃ ጩቤ አክርማ ቅጪ ጫጫ አገጬ ጭድ ጮቤ |
| **ጸ ጸ** | ኻያ ዘጠነኛ ። ፩/ ጰራቅሊጦስ = ጰራቅሊጦስ ። ጴጥሮስ = ጴጥሮስ ። ጰራቅሊጦስ እምጱ ጲላጦስ ጳውሎስ ጴጥሮስ ጵጵስና ቆጶስ ። |
| **ጸ ጸ ጠ፤** | ሠላሳኛ ። ፩/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ፪/ ጾመ = ጾመ ። ጸብሐ = ጠባ ። ፫/ ስሙ = ጽልመቱ ጸ ። ጸጋ ገጹ ቀራጺ ጻድቅ ጼዴንያ ጽጌ ጾመ |
| **ፀ ፀ ጠ፤** | ሠላሳ ኣንደኛ ። ፩/ የጽሑፍ ምሥጢር አደላዳይ ። ፪/ ፀሓይ = ፀሓይ ። ፅፍር = ጥፍር ። ፫/ ስሙ = ፀሓዩ ፀ ። ፀሓይ ብፁዕ ሠራፂ ነፃ ዓፄ ፅዱ ፆታ |
| **ፈ ፈ** | ሠላሳ ኹለተኛ ። ፩/ ፈርሀ = ፈራ ። ፈላ ፉቲ ፊና ፋታ ፌቆ ፍዳ ፎቅ |
| **ፐ ፐ** | ሠላሳ ሦስተኛ ። ፩/ የጳን መሠረታዊ ተግባር ለማስወገድ በመፍጨርጨር አገልግሎቱን ካውሮጳውያን ቋንቋዎች ለተወረሱ ቃላት ብቻ ለማድረግ ይጥራል ። |
| **ቈ ቈ** | ቈረ = ቈረ ። ቈስቈሰ = ቈሰቈሰ ። ቈላ ? ቍ ቋት ቌ ቍስል ? |
| **ኈ ኈ ኰ፤** | ኰሉ = ኍሉ ። ነኈለለ ? ኍ ኋላ ኌ ኍሉ ? |
| **ኰ ኰ ኈ፤** | ኰስሕ = ኰስ ። ኰሉ = ኍሉ ። ኰሰ ? ኲ ኳስ ኴ ኰስ ? |

| | |
|---|---|
| **ጐ ጐ** | ጐለተ = ጐለተ ። አንጐረጐረ = አንንጐራጐረ ። ጐሽ ? ጉ ጓዳ ዛጔ ጐዳይ ? |

**ማስገንዘቢያ**

**፩ኛ/** በምስክር ያልጸኑት ፊደላት ብቻ ባማርኛ ውስጥ ያላቸው አገልግሎት እስካኹን በተደረገው ጥናት አልተገለጸም ።

፪ኛ/ የጥያቄ ምልክት እየተደረገበት ጐሉ ፊደ እንደ ጐደለ አስተውል ።

| | |
|---|---|
| **ሉ ሉ** | የለ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ለ፤ ለኾኑ አናቅጽ) ። በላ = በሉ ። ጠላ = ጠሉ ። ፫/ ወይነ ተከሉ ። ወይንን ተከሉ ። |
| **ሙ ሙ** | የመ ካዕብ ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው መ ለኾኑ አናቅጽ) ። ሰማ = ሰሙ ። አለመ = አለሙ ። ፫/ ሕግ ፈጸሙ = ሕግን ፈጸሙ ። |
| **ሡ ሡ** | የሠ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ሠ ለኾኑ አናቅጽ) ። ነገሠ = ነገሡ ። ንጉሠ አንገሡ = ንጉሥን አነገሡ ። |
| **ሩ ሩ** | የረ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ረ ለኾኑ አናቅጽ) ። መራ - መሩ ። በር - በሩ ። ፫/ መሀሩነ = አስተማሩን ። |
| **ሱ ሱ** | የሰ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ሰ ለኾኑ አናቅጽ) ። መሳ - መሱ ። በሳ - በሱ ። ፫/ ብሉየ ሐደሱ = አሮጌን አደሱ |
| **ሹ ሹ** | የሸ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ለኾኑ አናቅጽ) ሸሸ - ሸሹ ። |
| **ቁ ቁ** | የቀ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ መድረሻቸው ቀ ለኾኑ አናቅጽ) ። በቃ - በቁ ። ነቃ - ነቁ ። ፫/ አውልዐ ሰጠቁ = ወይራን ሰነጠቁ ። |
| **ቡ ቡ** | የቀ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ መድረሻው በ ለኾኑ አናቅጽ) ። ጋለበ - ጋለቡ ። ደረበ - ደረቡ ። ፫/ ርኀበ አጽገቡ = የተራበን አጠገቡ ። |
| **ቱ ቱ** | የተ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ መድረሻቸው ተ ለኾኑ አናቅጽ) ። ገመተ - ገመቱ ። ፫/ መጽወቱ - መጸወቱ ። |
| **ኑ ኑ** | የነ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ መድረሻቸው ነ ለኾኑ አናቅጽ) ። በየነ = በየኑ ። ፫/ አድኅ ረኅኑ = አህያን ጫኑ ። የኸ ካዕብ ። ፩/ የአንደኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ለበስኩ = ለበስኹ ። |
| **ዙ ዙ** | የዘ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ መድረሻቸው ዘ ለኾኑ አናቅጽ) ። አዘዘ - አዘዙ ። ፫/ አዘዙነ = አዘዙን ። |
| **ዩ ዩ** | የየ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ መድረሻቸው የ ለኾኑ አናቅጽ) ። ገበየ - ገበዩ ። ፫/ ርእዩ = እዩ ። |
| **ዱ ዱ** | የደ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ደ ለኾኑ አናቅጽ) ። ወደደ - ወደዱ ። ፫/ ስግዱ = ስገዱ ። |
| **ጁ** | የጀ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) መሪ (መድረሻቸው ጀ ለኾኑ አናቅጽ) ። አበጀ - አበጁ ። |
| **ጉ ጉ** | የገ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) መሪ (መድረሻቸው ገ ለኾኑ አናቅጽ) ። መረገ - መረጉ ። ፫/ ዕጣነ አዕሩጉ = ዕጣንን አሳረጉ ። |
| **ጡ ጡ** | የጠ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) መሪ (መድረሻቸው ጠ ለኾኑ አናቅጽ) ። በለጠ - በለጡ ። ፫/ እብትረ ጸበጡ = በትርን ጨበጡ (ያዙ) ። |
| **ጩ** | የጨ ካዕብ ። ፩/ ሦስተኛ መደብ (ብዙ) መሪ (መድረሻቸው ጨ ለኾኑ አናቅጽ) ። ገጨ - ገጩ ። |
| **ጹ ጹ** | የጸ ካዕብ ። ፩/ ሦስተኛ መደብ (ብዙ) መሪ (መድረሻቸው ጸ ለኾኑ አናቅጽ) ። ቀረጸ - ቀረጹ ። ፫/ ወልደ ገሡጹ = ልጅን ገሡጹ (ቀጡ)፡ |
| **ፉ ፉ** | የፈ ካዕብ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) መሪ (መድረሻቸው ፈ ለኾኑ አናቅጽ) ። ጻፈ - ጻፉ ። ፫/ ዘርቤተ ሰላም ነጻፉ = የፍቅር ምንጣፍን አነጠፉ ። |
| **ሚ** | የመ ሣልስ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ብዙ) መሪ (መድረሻቸው መ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ሳመ - ሳሚ ። ፫/ መድረሻቸው መ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ደገመ - ድገሚ ። |

| | |
|---|---|
| ሢ | የሠ ሣልስ ። ፩/ መድረሻቸው ሠ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ነገሠ - ነጋሢ ። |
| ሪ | የረ ሣልስ ። ፩/ መድረሻቸው ራ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። በራ - በሪ ። ፫/ መድረሻቸው ረ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ሰበረ - ስበሪ ። |
| ሲ | የሰ ሣልስ ። ፩/ መስተፃምር ። ኼደ - ሲሔድ ። |
| ሺ | የሸ ሣልስ ። ፩/ መድረሻቸው ሠ፤ ሰ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ነገሠ - ንገሺ ። ለበሰ - ልበሺ ። |
| ቂ | የቀ ሣልስ ። ፩/ መድረሻቸው ቀ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። በቃ - በቂ ። ፫/ መድረሻቸው ቀ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ሰበቀ - ስበቂ ። |
| ቢ | የበ ሣልስ ። ፩/ መድረሻቸው በ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ገባ - ገቢ ፫/ መድረሻቸው በ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ገባ - ግቢ ። |
| ኪ | የከ ሣልስ ። ፩/ መድረሻቸው ከ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ላከ - ላኪ ። ፫/ መድረሻቸው ከ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ላከ - ላኪ ። |
| ዊ | የወ ሣልስ ። ፩/ መድረሻቸው ዋ ከኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ለዋለዊ ። ፫/ መድረሻቸው ወ ከኾኑ አናቅጽ ትእዛዝ አንቀጽን መወሰኛ ። ሠዋ - ሠዊ ። |
| ሃ | የሀ ራብዕ ። ፩/ የአህያ ማናፋት ። አህያ ሲያናፋ ሃ! ሃ! ሃ! ይላል ። |
| ላ | የለ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በላ ። |
| ማ | የመ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ገማ ። |
| ሣ | የሠ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ነሣ ። |
| ራ | የረ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ኰራ ። |
| ሳ | የሰ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ በሳ ። |
| ሻ | የሸ ራብዕ ። ፩/ የሠ፤ ሰ ምትክ ነገሠ - መናገሻ ። ቀደሰ - መቀደሻ ። ፫/ ፈለገ ። ዕቃ ይሻል ። ወንድሙን ይሻል ። ፬/ ተሰራጨ ። የበላኹት ምግብ ገና ሻ አላለልኝም ። |
| ቃ | የቀ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በቃ ። ፫/ ደረቀ፤ ቀነበረ ። እንጀራውን ቃ አላደረገችውም ። |
| ባ | የበ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ገባ ። ፫/ የበግ ጩኸት ። በጊቱ በግ ወልዳ ባ! ባ! ባ! ትላለች ። |
| ታ | የተ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። መታ ። |
| ቻ | የቸ ራብዕ ። ፩/ የተ ምትክ ። ዘመተ - ዘመቻ ። |
| ና ነዓ | የነ ራብዕ ። ፩/ የመጣ ትእዛዝ አንቀጽ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ወደ እዚኽ ና ። ፫/ ጭምር ። እርሱና እኔ መጥተን ነበር ። |
| ኛ | የኘ ራብዕ ። ፩/ የነ ምትክ ገመነ - መግመኛ ። ፫/ ባዕድ መድረሻ ። አማራ - አማርኛ ። |
| አ | የአ ራብዕ ። ፩/ ውጋት የያዘው ሰው ሲያቃስት የሚያሰማው ድምጽ ። ኣ! ኣ! እንዳለ አደረ ። |
| ካ | የከ ራብዕ ። ፩/ እርባታ መሪ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ቦካ ። |
| ዋ | የወ ራብዕ ። ፩/ ዋ አለማወቅ...... ዋ ትነካውና! ዋ ልጅነት! ፫/ እርባታ መሪ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ። ለዋ ። ፬/ አገናዛቢ ተውላጠ ስም ። ንብረትዋ ። ፭/ ማቈላመጫና ማጕላመሻ ። እናቴዋ ። ወንድሜዋ ። |
| ዛ | የዘ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ገዛ ። |
| ዣ | የዠ ራብዕ ። ፩/ የዘ ምትክ ። ገዛ - መግዣ ። |
| ያ | የየ ራብዕ ። ፩/ አመልካች ። ያ ሰው ። ፫/ እርባታ አከናዋኝ ። ያመጣል ። |
| ዳ | የደ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ከነዳ ። |
| ጃ | የጀ ራብዕ ። ፩/ የደ ምትክ ። ከነዳ - መከንጃ ። |

| | |
|---|---|
| **ጋ** | የገ ራብዕ ። ፩/ ሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ዘጋ ። ፪/ ዘንድ ። እኔ ጋ ነው (ጸያፍ) ። |
| **ጣ** | የጠ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ወጣ ። |
| **ጫ** | የጨ ራብዕ ። ፩/ የጠ፤ የጸ ፀ ምትክ ። ጋጠ - መጋጫ ። ቀረጸ - መቅረጫ ። ዐመፀ - ማመጫ ። |
| **ፋ** | የፈ ራብዕ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። አለፋ ። |
| **ቋ** | የቈ ራብዕ ። ፩/ ዕንጨት ወይም ዕቃ ሲሰበር የሚያሰማው ድምጽ ። ቋ ሲል ሰማኹ ። ፪/ የሣር ዓይነት ። |
| **ኳ** | የኰ ራብዕ ። ፩/ ተንኳኳ (ለኣንደዪ) ። ኳ ሲል ሰማኹ ። |
| **ጓ** | የጐ ራብዕ ። ፩/ ተንጓጓ (ለኣንዳዪ) ። ጓ ሲል ሰማኹ ። ፪/ የያልፈነዳ አበባ ። |
| **ሌ** | የለ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ። አመል - አመሌ ። |
| **ሜ** | የመ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ። ስም - ስሜ ። |
| **ሤ** | የሠ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ንጉሥ - ንጉሤ ። |
| **ሬ** | የረ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ። ሰፈር - ሰፈሬ |
| **ሼ** | የሸ ሓምስ ። ፩/ የየ ምትክ ። ጋሻ - ጋሻዬ - ጋሼ ። |
| **ቄ** | የቀ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ። ወርቅ - ወርቄ ። |
| **ቴ** | የተ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ። ቤት - ቤቴ ። |
| **ቼ** | የቸ ሓምስ ። ፩/ ያንደኛ ። መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በርትቼ ። ፪/ ፈረስን ኺድ፤ ኺጂ የማያ ቃል ። |
| **ኔ** | የነ ሓምስ ። ፩/ የስም መወሰኛ ። መነነ - ምናኔ ። ፪/ (አገናዛቢ) ወገን - ወገኔ ። |
| **ኜ** | የኘ ሓምስ ። ፩/ የነ ምትክ ። (ኣንደኛ መደብ ነጠላ) ። ኹነ - ኹኜ ። |
| **ዔ** | የዐ ሓምስ ። ፩/ የዕብራውያን ፊደል ። ፪/ ስመ አምላክ ። |
| **ዜ** | የዘ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ። ጋዝ - ጓዜ ። |

| | |
|---|---|
| **ዬ** | የየ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ ። ዕቃ - ዕቃዬ ። ፪/ ወሳኝ ሰውዬው መጣ ። ፫/ ኃዘንን መግለጫ ። |
| **ጌ** | የገ ሓምስ ። ፫/ ቅጽልን መወሰኛ ። ባለገ - ባለጌ ። ፫/ (አገናዛቢ ኣንደኛ መደብ ነጠላ) ። በግ - በጌ ። |
| **ጤ** | የጠ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ (ኣንደኛ መደብ ነጠላ) ። ጌጥ - ጌጤ ። የጠ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ (ኣንደኛ መደብ ነጠላ) ። ጌጥ - ጌጤ ። |
| **ጬ** | የጨ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ (ኣንደኛ መደብ ነጠላ) ። አገጭ - አገጬ ። |
| **ጼ** | የጸ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ (ኣንደኛ መደብ ነጠላ) ። ገጽ - ገጼ ። |
| **ፌ** | የፈ ሓምስ ። ፩/ አገናዛቢ (ኣንደኛ መደብ ነጠላ) ። አፍ - አፌ ። ፪/ የዕብራውያን ፊደል ። ፫/ ስመ አምላክ ። |
| **ም** | የመ ሣድስ ። ፩/ ደግሞ ። አንተም ተጣላኸኝ ። ፪/ የአሉታ ምግባር የአናቅጽ ባዕድ መድረሻ ። በላ - አልበላም ። ፫/ የምዕራፍ ክፊል ስም ። |
| **ስ** | የሰ ሣድስ ። ፩/ መስተፃምር ። እኔ ስመለስ አንተ ስትበላ መጣ ። ፪/ እንክንን ገላጭ ። ወንድምስ አለኝ ። ሰውስ ባይፈጠር ይሻለው ነበር ። ፫/ አበላላጭ ። እሱስ አያምርም ። |
| **ሽ** | የሸ ሣድስ ። ፩/ የሡ፤ ሰ፤ ምትክ ነገሠ - ነጋሽ ። ቀደሰ - ቀዳሽ ። |
| **ብ** | የበ ሣድስ ። ፩/ መስተፃምር ። ብመጣ መልካም ነበር ። |
| **ች** | የቸ ሣድስ ። ፩/ የተ ምትክ ። ደረተ - ደራች ። |
| **ን** | የነ ሣድስ ። ፩/ የተጠቃሽ ተሳቢ ምልክት ። ጌታኩንን አየኹት ። ፪/ የጥያቄ ምልክት ።ትመጣለኸን? ፫/ የኣንደኛ መደብ (ብዙ) እርባታ መሪ ። እንመጣለን ። |
| **ኝ** | የኘ ሣድስ ። ፩/ የነ ምትክ ። መነነ - መናኝ ። ፪/ የኣንደኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በላኝ ። ነከሰኝ ። |
| **እ** | የአ ሣድስ ። ፩/ ያንደኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ ባዕድ መነሻ ። እመጣለኹ ። ፪/ መስተዋድድ ። እቤቱ አጠገብ አገኘኹት ። |

| | |
|---|---|
| **ክ** | የከ ሣድስ ። ፩/ የኹለተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ (መድረሻቸው ከ፤ ለኾኑ አናቅጽ) ። ባረከ - ባርክ ። ሰበከ - ስበክ ። |
| **ኽ** | የኸ ሣድስ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። በላእከ = በላኽ ። |
| **ው** | የወ ሣድስ ። ፩/ አገናዛቢ (ሦስተኛ መደብ ነጠላ) ። በወሬ ሞተበት ። ፫/ ወሳኝ ። ሰውዬው መጣ ። ፩/ የሦሰኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። ወሰደው ። |
| **ዠ** | የዠ ሣድስ ። ፩/ የዘ ምትክ ። ገዛ - ገዠ ። |
| **ይ** | የየ ሣድስ ። ፩/ የሦስተኛ መደብ (ነጠላ) እርባታ አከናዋኝ ። ይምጣ ። ፫/ መድረሻቸው ለ፤ ለኾኑ አናቅጽ ቅጽልን መወሰኛ ። ገደለ - ገዳይ ። ጐደለ - ጐዳይ ። |
| **ጅ** | የጀ ሣድስ ። ፩/ የደ ምትክ ። አረደ - አራጅ ። |
| **ጭ** | የጀ ሣድስ ። ፩/ የጠ ምትክ ። ጠጣ - ጠጭ ። |
| **ቌ** | የቍጥር ከፊለ ስም ። |
| **ሆ** | የሀ ሳብዕ ። ፩/ የጭፈራ አዝማች ። ሆ! እንዳሉ ዋሉ ። ሆያ ሆዬ! ። |
| **አ** | የአ ሳብዕ ። ፩/ አገናዛቢ (ባክብሮት) ። ሥራዎ ለዚሕ አበቃዎ ።፫/ የኹለተኛ ። መደብ (ነጠላ) እርባታ መሪ ። እለምንዎታለኹ ። |
| **ዮ** | የየ ሳብዕ ። ፩/ አንቺ ። ሴትዮ ። |
| **ለየ ሌለየ** | ነጠለ ። ገበሬው ምርትን ከግርድ ለየ ። ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓመትም አይቄዩ ። ፩/ ዐወቀ ። ሕፃኑ ፊደልን (እናቱን) ለየ ። ፫/ አወገዘ ። ሊቀ ጳጳሳቱ መናፍቁን በጴጥሮስና በጳውሎስ ሥልጣን ለየው ። |
| **ለየ** | በስም መነሻ እየገባ የግልነትን የሚገልጽ ። ለየራሳችን ለየጥቅማችን ። |
| **መሸ መስየ** | ቀን አልፎ ሌሊት ተተካ ። እውነትን ተናግሮ፤ እመሸበት ያድሩዋል ። እንዴት አመሸኽ? እንደምን አመሸኽ? |

| | |
|---|---|
| **ረጨ ረቀየ ፈነጠቀ** | ቄሱ ጠበልን ረጨ ። እጣቢውን ወደ ውጭ እርጨው ። |
| **ሰጠ** | መጸወተ ። ገንዘቡን ለድኻ ሰጠ ። ፩/ ቸረ ። መጽሐፉን ለወዳጁ ሰጠ ። ፫/ አወረሰ ። እገሌ ሲሞት መላ ንብረቱን ለሚስቱ ሰጠ ። ፬/ አጋለጠ ። ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ ሰጠ ። ፭/ እንካ አለ ። ያልሰጡት ተቀባይ ያልጠሩት አቤት ባይ ። |
| **ሸሸ** | ሮጠ (በፍርሃት) ሙክቱ ቀበሮውን አይቶ ሸሸ ። ነገርን ሸሸ ። የሚሸሹበትን አምባ፤ ሲሸሽ ተገኘ ። |
| **ሸተ ሰወየ** | ለመብል የደረሰ ፍሬን አፈራ ። የዘረዘረው ስንዴ ሸተ ። ወይኑ ሸተ ። |
| **ሸጠ ሤጠ** | በዋጋ ለወጠ ። በጉን ሸጠ ። ሸቀጡን ሸጠ ። ይሁዳ ክርስቶስን ሸጠ ። ግዛኝ ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ ። |
| **ቀረ** | ተረፈ ። ከሓምሳ ሙክቶች አንድ ብቻ ቀረ ። ከዓሥር በሽተኞች አንድ ብቻ (ከሞት) ቀረ ፩/ ከመኼድ አመለጠ ። ወደ ጦርነት ከመሔድ ቀረ ። ፫/ ተተወ፡ ወይ ጋሻ ቀድሞ ቀረሻ ። ሥጋ ቀረ ። ዕዳ ቀረ ። |
| **ቀጨ** | ነቀለ (ከአንጓው) አክርማን ቀጨ ። ፩/ አቃወሰ ። ትራሱ አንገቱን ቀጨው ፫/ በአጭር አስቀረ፤ ቀሠፈ ። በልጅነቱ ቀጨው ። ፬/ ሰነጠቀ (ሰውነትን) የጥቅምት ብርድ ይቀጫል ። |
| **በጀ** | መልካም ኾነ፤ እንኳን ። መምጣቱ በጀን ። የክርስቶስ መስቀል በጀን ። አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው ። የሚበጀውን፤ ባለቤት ያውቃል ። ፩/ እሺ፤...... በጀ! ከዚያስ በኋላ? |
| **ተቸ** | አፍታታ፤ ተንትኖ ተናገረ ። (ከሳሽና ተከሳሽ ከተናጋገሩ በኋላ፤ እንዲኽ ያላችኹት እንዲኽ ማለታችኹ አይደለምን? እያሉ በተጣራ አማርኛ መጠየቅ - በዳኝነት ወይም በሽማግሌነት) እገሌ ዛሬ እንዴት አድርጎ ተቸ እባክኽ! ፩/ ነቀፈ ። መሥራቱ የለ ቁጭ ብሎ ይተቻል ። ፫/ ነውርን ስሕተትን እንከንን ጉድለትን አሳየ ተናገረ፤ አመለከተ ። ስለ ጨዋታው የቀረበልን ትች እምብዛም አስጊ አይደለም ። |

| | |
|---|---|
| **ተወ** | አቆመ ። ትምህርትን ተወ ። ጠጅ መጠጣትን ተወ ። ፪/ አስቀረ ። ያምራል ብለው ከተናገሩት ይከፋል ብለው የተውት ። ፫/ ይቅር አለ ። ኃጢአቱን በደሉን ተወለት ። ፬/ ጣለ ። ንብረቱን ትቶ ኼደ ። |
| **ቸረ ተኼረወ** | ለገሠ ። ሀብታቸውን ለድኻ ይቸራሉ ማለትን ሰማኹ ። በሙቅ ውኃ የታጠበ፤ በሰው ገንዘብ የቸረ ። |
| **ቸከ** | ነገር፤ ለዛና ውሳኔን አጣ ። አኹንስ ነገርኽ ቸከኝ አለው ። |
| **ቸኸ** | ጥርስ እድፋም ኾነ ። ጥርሱ ቸኸ ። |
| **ነጨ ነጸየ** | ነቀለ ። ጠጕሩን ነጨ (በንዴት) ፪/ መለጠ፡ ፊቱን ነጨ ። ፫/ ቦተረፈ ኀርቡ ከአህያው ቂጥ ነጨለት ። |
| **አለ** | እንዲኽ ተናገረ ። ክርስቶስ ተከታዮቹን ኹሉ እርስ በርሳችኹ ተፋቀሩ አለ ። ያልወለድኹት ልጅ አባቴ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ ። ይወደዋል ካሉ ይመከረዋል ይወልደዋል ካሉ ይመስለዋል ። ዝም አለ ። ቀስ አለ ። ስብርብር አለ ። እንኩትኩት አለ ። ፪/ መሰለ፤ ተባበረ (በጣዕም) ። ማር፤ ማር ይላል ። ወተት ወተት ይላል ። |
| **አለ ሀለወ** | አልሞተም ። ይኖራል ። እንምደን አለኽ? እገሌ ሞተ? ኧረ አለ ። ፪/ አልኼደም ። እገሌ ወደ ጐንደር ኼደ? ኧረ አለ ። ፫/ ጸጋ እንዳለው ገላጭ፤ አሰረጅ ። ቤት አለኝ ። ገንዘብ አለኝ ። |
| **አለ** | ወደ አሉታ ምግባር መለወጫ ። መኼድ - አለመኼድ ማልቀስ - ቤት አለ ኣጥር፤ ሰው አለልብስ ። ቤት አለ ሴት፤ ከብት አለበረት ። አለማረፍ የተርብ ቤት መቀስቀስ ። |
| **አሸ ሐሰየ** | በእጁ ምርቅንና ገለባን ከፍሬ ለየ ። ያልተፈለገውን የገብስ ቆሎ ለእናቱ አሸ ። ፪/ አካል ልብስ እድፋን እንዲለቅ አፍተለተለ ። በሣሙና የተመታውን ልብስ አሸ ። ፫/ ቡኣ የወረደውን፤ አካሉ የጓጐለውን የጓጐለው እንዲበተን አፍተለተለ ። የኔታውን እግር አሸ ። ፫/ አለፋ ። ቆዳን በሞራ አሸ ። ፭/ ደበደበ ። ለአምስት ኾነው አሹት ። |
| **አበ አብ** | አባት ። ፪/ በትውልድ ዘፍ ሳይኾን በዘመን ብዛት ከፍ ላለ ሰው የሚሰጥ የአክብሮት ስም ። አበ፤ እንደምን ዋሉ? |

| | |
|---|---|
| **አዠ** | የዘንጋዳ ውኃ የመሰለ ከቍስል ውስጥ ፈሰሰ ። የእገሌ ቍስል አዠ ። ፪/ ጥቂት በጥቂት አፈሰሰ (አዲስ የሸክላ ዕቃ) ። አዲሱ እንስራ አዠ ። |
| **አየ ርእየ** | ተመለከተ፤ አስተዋለ ። የጐረቤት ሴባ፤ ቢያዩት ይስቅ ባያዩት ይሰርቅ ። እያየኋት የምታስቀኝ ሚስት አገባኹ ። ፪/ ተቀበለ ። መከራውን አየ ። ፫/ ተገናኘ፤ ተጋጠመ ። በዓይነ ሥጋ ለመተያየት ያብቃን ። |
| **አጨ ሐጸየ** | ለሚስትነት መርጦ ተዋዋለ ። ይኽ ጐበዝ ይኽችን ቈንጆ አጨ ። ፪/ መረጠ ። ላስተዳዳሪነት አጨው ። |
| **ኧረ** | አዬ! እገሌ ኼደ ። ኧረ ። |
| **ኧኸ** | እንዴ! ኧኸ! ምን ማለቱ ነው? |
| **ከመ ከመ** | እንደ ከመ ቅጽበተ ዓይን ። ውጉዝ ከመ አርዮስ ። |
| **ከነ ከ -** | እነ አጓዳኝ አብዥ ። መስፍን ከነአስፋ ጋራ ኼደ ። |
| **ወደ** | የመድረሻ መስተዋድድ ። ወደ ዘማ ቤት መዝለቅ መጥፎ ጠንቅ ። |
| **ጀለ** | እንከፍ ኾነ ። የእገሌ ልጅ ምነው እንዲኽ ጀለ? |
| **ጨሰ ጤሰ** | በደንብ ካለመንደዱ የተነሣ ወደ ጥቍር ተናኝነት ተለወጠ ። ርጥብ ዕንጨት ይጨሳል ። ፪/ ገመነ ። በነገሩ ጨሰ ። |
| **ጨቀ** | መሬቱ ውኃ ከመጠጣቱ የተነሣ የተንቈረዘዘ ጨፌ ኾነ ። አኹንስ ሜዳው ኹሉ ጨቀ ። |
| **ፈጀ** | አቃጠለ ። እሳት ፈጀው ። ቡና ፈጀው ። ፪/ ፈጸመ፤ አገባደደ ። የባለጌ ልጅ መንገድ ይፈጅ ነገር አይፈጅ ። ፫/ ገደለ ። ሕዝቡን በሽታ ፈጀው ። ፬/ ጨረሰ ። ገንዘቡን በመሸታ ፈጀው ። ነገረ - ፈጅ = ጠበቃ ። ፍየለ - ፈጅ = የተክል ዓይነት ። |
| **ፈጨ** | በክክነት፤ በክርትፍነት በጕርሶነት በስልቅነት፤ ከግዙፍ ገላ ወደ በናኝ ገላ በወፍጮና በመጅ መሣሪያነት፤ ለወጠ ። ሓምሳ ዳውላ እኽል በአንድ ቀን አዳር ፈጨ ። የትም አምጪው ዱቄቱን አምጪው ። እኽል ሲጠፋ ወፍጮ ይሰላል ። እኽል ሲገኝ ወፍጮ ይመዋልጣል ። |

| | |
|---|---|
| **ቈረ ቈረ** | ቀዘቀዘ፤ በረደ፤ ዛሬ ምነው በአያሌው ቈረ? |
| **ቈየ** | ዘገየ ምነው እገሌ ቈየ? ፪/ ጠበቀ ። ቈየኝ መጣኹ ። |
| **ቈጨ** | ልቡናን በላ፤ ምነው ባደረግኹት ወይም ባላደረግኹት ኖሮ አለ ። ነገሩ ቈጨው ። |
| **ኰሰ ኰሐሰ** | ፍጋም ኾነ ። ይኽ ቦታ ኰሰ ። የተከመረው ቍሻሻ ኰሰ ። |
| **ጐሸ** | ደፈረሰ ። ምነው ይኽ ጠላ ጐሸ? |
| **ሀሁ** | የአማርኛ ፊደላት መጠሪያ ። ምን ትማራለኽ? ሀሁን እማራለኹ ። ሀሁ ሳይሉ ጽሕፈት ውል ሳይዙ ሙግት ። |
| **መዪ** | የዓፄ ቴዎድሮስ የፈረስ ስማቸው መይሳው፤ አንበሳው እንደ ማለት ነው ። |
| **አዉ** | የኸርብ ጩከት ። ፪/ ኸርብ ። አዉ መጣ ። (ለሕፃን የሚነገር) |
| **የጁ** | በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ አገር ። |
| **ለሚ** | የሚለማ ። ለሚ መሬት ። ለሚ አትክልት ። |
| **ለኪ** | የሚለካ ። መሬት ለኪ ። ዘይት ለኪ ። ልብስ ለኪ ። |
| **ለጊ** | የሚለጋ ኳስ ለጊ ። ሩር ለጊ ። ፪/ ጠጭ (በብዙው) ። ጠላን ለጊ ። |
| **ለፊ** | የሚለፋ ። ለፊ ቍርበት ። ለፊ ሰው ። |
| **መሪ** | የሚመራ ። ዕዉር ሲወበራ ከመሪው ይጣላል፤ ወይም ይወረውራል ። ፪/ አለቃ ። ለመሪኽ ዓሣ ምስል ። ፫/ ጠቋሚ ። የጠላት መሪ ነበር ። ፬/ መሪ - ዜማን በሥርዓት የሚያስዜም የሚመራ የሚነቀነቅ ። ዜማ እንዳይሰበር መጠበቅ የመሪጌታ ልዩ ተግባር ነው ። |
| **ሠሪ** | የሚሠራ ። ሸክላ ሠሪ ። ቤተ ሠሪ ። መስተዋት ሠሪ ። ነገረ ሠሪ የገባበት ትዳር፤ ቢወድም እንጂ አይደረጅም ። ወጠ ሠሪ ። ሽሩባ ሠሪ ። |
| **ሠዊ** | የሚሠዋ ። ራሱን ስለ ወገኖቹና ስለ ሀገሩ ሠዊ የኾነ፤ የክብርን አክሊል ይወርሳል ። |
| **ረቢ** | የሚረባ ። ዘረ ረቢ ከኮነች ስንኳን በ፳ ብር፤ በ፻ም ትገዛ ። |
| **ረቢ ረቢ** | መምህር ። «ረቡኒ»? |
| **ረኪ** | የሚረካ ። ጠጥቶ ረኪ ያልኾነ ይገኛልን? |
| **ረጊ** | የሚረጋ ። ከአንድ ረጊ ። ረጊ ከብት ። ረጊ ወተት ። |
| **ሰሚ** | የሚሰማ ። ውል ሰሚ ። ምክር ሰሚ ። አሉባልታ ሰሚ ። በደል ሰሚ ። አቤቱታ ሰሚ ። ልቅሶ ሰሚ ። ተናጋሪ ሲያመርት፤ ሰሚ ያከማቻል ። |
| **ሰቢ** | የሚሰባ ። ሰቢ ከብት አካሉ ሰቢ ነው ። |
| **ሰኪ** | የሚሰካ ። የነገረ ሰኪን ሕንፃ፤ ያለ ትዕግሥት የሚንደው የለም ። ሳጋ ሰኪ ። ብርጭቆ ሰኪ ። መጫሚያ ሰኪ ። |
| **ሰጊ** | የሚሰጋ ። እንደ እገሊት ለንብረት ሰጊ የትም አይገኝ ። ሰጊ ናት ። ሰጊ ነው ። |
| **ሰፊ** | የሚሰፋ ። ከሰፊ ቤት እራፊ አይታጣም ። መጫሚያ ሰፊ ። ኮርቻ ሰፊ ። |
| **ሰፊ** | የሰፋ ። ሰፊ መጫሚያ፤ ሰፊ ቤት፤ ሰፊ ልብስ፤ ሰፊ አገር ። በሰፊው ሜዳ ላይ እንደ ልብ ጉግስን መጫወት ይቻላል ። ሆደ ሰፊ ። ልበ ሰፊ ። |
| **ቀሚ** | የሚቀማ ። የሰውን ገንዘብ ቀሚ ። የድኻን ሀብት ቀሚ ። |
| **ቀሪ** | የሚቀር፤ የቀረ፡ ከደሞዝኽ ቀሪው ስንት ነው? ቀሪ ገንዘብ ። ቀሪ ሰው ። |
| **ቀቢ** | የሚቀባ ። ቅቤ፤ ነውር ቅቤ ። ቀለም ቀቢ ። ኖራ ቀቢ ። ዘይት ቀቢ ። ሥዕል ቀቢ ። |
| **በሪ** | የሚበራ ። በሪ ጠዋፍ ። በሪ ኩራዝ ። በሪ ፋኖስ ። |
| **በቂ** | የሚበቃ ። ለክርክርኽ በቂ ማስረጃን ማቅረብ ይገባኻል ። በቂ ነገር ። በቂ ነው ። በቂ ደሞዝ ። በቂ ችሎታ ። በቂ ቅጽል ። በቂ ጦር ። በቂ መሣሪያ ። በቂ ወታደር ። በቂ ሥራ ። በቂ ገንዘብ ። |
| **ተኪ** | የሚተካ ። በጐደለው ተኪ ነው ። ነገርን ተኪ ። በጠፋው ተኪ ። |
| **ተጊ** | የሚተጋ ። ለሕመምተኛ ተጊ ነው ። ለንብረት ተጊ ናት ። ለሥራ ተጊ ነው ። |
| **ተፊ** | የሚተፋ ። የጐረሰውን ተፊ ። የተበደረውን ተፊ ። ተፊው እርሱ ነው (ለቡዳ) ። አክታን ተፊ ። ጠጥቶ ተፊ ። |

| | |
|---|---|
| **ነቂ** | የሚነቃ ። ከእንቅልፉ ነቂ ። እገሌ ነቂ ነው = ጠርጣሪ ። መረሬ ነቂ ነው ። ነቂ እግር ። |
| **ነኪ** | የሚነካ ። እንደ እገሌ ሰውን በነገር ነኪ አለ ብለኸ አትጠራጠር ። ነኪ ኮርቻ ። የሰውን ዕቃ ነኪ ። |
| **ነጊ** | የሚነጋ ። ከመከራው ጽናት የተነሣ ሌሊቱ ነጊም አልመለሰን ነበር ። |
| **ነፊ** | የሚነፋ ። ጥሩንባን ነፊ ። ዋሽንትን ነፊ ። ላስቲክን ነፊ ። ኳስን ነፊ ። ወሬን ነፊ ። |
| **ከኪ** | የሚከካ ። ባቄላን ከኪ ። አተርን ከኪ ። ጠላን፤ ጠጅን ከኪ ። |
| **ከፊ** | የሚከፋ ። ከፊ መኾንዋ አይጠረጥርም ። |
| **ወቂ** | የሚወቃ ። ጤፍን ወቂ ። ተልባን ወቂ ። ሰውን ወቂ ። |
| **ወጊ** | የሚወጋ ። ወጊ ጦር ። እግርን ወጊ እሾኽ ። ሰውን ወጊ ዐይን አለው ። |
| **ዘሪ** | የሚዘራ ። ዘሪው ጣቴ ። ምድሩ ያባቴ ። እኽልን ዘሪ ። ዘሪ ሊዘራ ወጣ ። |
| **ዘቢ** | የሚዘባ ። ዘቢ ምሰሶ ። ዘቢ መዝጊያ ። ዘቢ ማዕዘን ። |
| **ዘጊ** | የሚዘጋ ። በርን ዘጊ ። ዘሃን ዘጊ ። ልሳን ዘጊ ። |
| **የሚ** | ይአናቅጽ ባዕድ መነሻ ። መጣ - የሚመጣ ። ኼደ - የሚኼድ ። |
| **የዪ** | አንበሳ አይቋቋማትም የምትባል የትንሽ ትልቅ አውሬ ። ጥንት፤ የዪን ገዳይ ትልቅ ክብር ነበረው ። |
| **ደሚ** | የሚደማ ። ደሚ አካል ። ደሚ ቊስል ። |
| **ደቂ** | የሚደቃ ። ደረት ደቂ ። |
| **ደፊ** | የሚደፋ ። እኽልን ደፊ ። ሰውን ደፊ ። ፈሳሽን ደፊ ። ቊሻሻን ደፊ ። |
| **ገሚ** | የሚገማ ። ገሚ ቊስል ። ገሚ ሰውነት ። ገሚ ሽቶ ። |
| **ገሪ** | የሚገራ ። በቅሎን ገሪ ። ፈረስን ገሪ ። ባለጌን ገሪ ። |